# የፍቅር እመቤት

እንደወርቅ እንደ አልማዝ ጊዜ የማይለውጣት፤
በሙሉ ተግባሯ ፍቅር የሞላባት፤
የማይሰለችና የማይጠግብ ልዩ ተፈጥሮ አላት።

ከመቀበል መለገስ በጣም ትወዳለች፤
በብዙ ሥራዋ ሰውን ታስደስታለች፤
ትንሽ ትልቅ ሳትል ሁሉን ታፈቅራለች።

በፀባይ ላይ ውበት ደርቦ ሰጥቷታል፤
ተፈጥሮዋንም አይቶ አገር ያደንቃታል፤
ቀርባ እንድታጫውተው ሁሉም ይመኛታል።

ይህች የፍቅር ፏፏቴ ምንጯ ያልታወቀው፤
የሷ ነው ባንዲራው ልቤ የተተከለው፤
ሌት ተቀን ነው በውስጤ የሚውለበለበው።

በበረደኝ ጊዜ የፍቅሯ ማገዶ ነዶ የሚያሞቀኝ፤
በደከመኝም ጊዜ የፍቅሯ ከዘራ ድጋፍ የሚሰጠኝ፤
አለችኝ ይህች ልዩ ሰው በጣም የምታኮራኝ።

የኑሮዬ ደስታ ይህች የፍቅር እመቤት፤
እንደ እናት እንደ እህት እጅግ የምወዳት፤
ከእግዜር ያገኘኋት ስጦታዬ ጓደኛዬ እኮ ናት።

ከ ኒኒ ለገሰ